የዐማራ ሕዝብ የህልውና አደጋ መንስኤና መፍትሔው

የህልውና አደጋ (Existential Threat) ምንድን ነው ?

የዐማራን ሕዝብ የህልውና አድጋ መንስኤና ስለ መፍትሄው ከማውሳቴ በፊት የህልውና አደጋ ማለት ምን ማለት እንደሆነ እንመልከት ። የህልውና አደጋ (Existential Threat) ማለት የአንድ ማህበረሰብ ፣ ሕዝብ ፣ ሀገር ወይንም የሰው ልጅ አጠቃላይ ደህንነቱ ፣ ቀጣይነቱ እና በህይወት መኖሩ ሙሉ በሙሉ ሊጠፉ የሚችሉበት ከፍተኛ አደጋ ላይ መውደቅ ማለት ነው ። ይህ አድጋ ከአንድ ተራ አደጋ የሚለየው ማህበረሰቡ እንደ አንድ ወጥ አካል ማንነቱን (identity) ይዞ የመኖር ዕድሉን ጨርሶ የሚያሳጣው መዋቅራዊ ስጋት መሆኑ ነው ።

አንድን አደጋ „የህልውና አደጋ“ የሚያሰኙ ዋና ዋና መገለጫዎች ፡-

1. ዳግም እንዳያገግም ወይንም እንዳያንሰራራ ማድረግ ፡-

ከአደጋው መከሰት በኋላ ማህበረሰቡ ተመልሶ ወደ ነበረበት ማንነቱ ወይንም ኑሮው መመለስ እንዳችል ማድረግ ።

2. ማንነትን ማጥፋት፡-

ሕዝቡ ቋንቋው ፣ ባህሉ ፣ ታሪኩና ማህበራዊ እሴቶቹ ሙሉ በሙሉ እንዲጠፉ ወይም እንዲቀይሩ መገደድ ።

3. በህይወት የመኖር መብት መግፈፍ ፡-

በጅምላ ጭፍጨፋ ፣ በረሃብ ፣ በበሽታ ወይም በማፈናቀል ምክንያት የሰዎች ህይወት እንዲያልፍ ማድረግ ።

የህልውና አደጋ ዓይነቶች ፡-

1. ማህበራዊና ፖለቲካዊ አደጋ ፡-

በአንድ ማህበረሰብ ላይ የሚታወጅ የዘር ማጥፋት (Genocide) ፣ የማንነት ማጥፋት (Cultural Erasure) ወይም ከቄያቸው የማፈናቀል ፖሊሲ ።

2. ተፈጥሮአዊና አካባቢያዊ አደጋ ፡-

በአየር ንብረት ለውጥ ፣ አስከፊ ድርቅ ወይም የምግብ ዋስትና እጦት ያሉ አደጋዎች የሚያስከትሉት አደጋዎች።

3. ዓለም አቀፋዊ አደጋዎች ፡-

መላውን የሰው ልጅ ህልውና አደጋ ላይ የሚጥሉ እንደ ኒውክሌር ጦርነት ወይም አስከፊ ወረርሺኞች ያሉ አደጋዎች ናቸው ።

በአጠቃላይ የህልውና አደጋ ነገ የመኖርን እና በህይወት የመቀጠል ዋስትና ሙሉ በሙሉ ጥያቄ ውስጥ የሚከት ትልቅ ስጋት ነው ። የዐማራ ሕዝብ ያጋጠመውና የአልሞት ባይ ታጋድሎ በማድረግ ላይ የሚገኝበት መሰረታዊ ምክንያት እነዚህ ከላይ ከተጠቀሱት ውስጥ አንዱ የሆነው ማህበራዊና ፖለቲካዊ አደጋ ስለ ኢጋጠመው እሱን በማስወገድ ከፈጣሪ የተሰጠውን በህይወት የመኖር መብቱን ለማረጋገጥ ነው ።

በዐማራው ሕዝብ ላይ የተከፈቱ ዘርፈ ብዙ የህልውና አደጋዎች ፡-
1. በብሔር ማንነቱና ዕምነቱን መሠረት ያደረጉ ጥቃቶችና ጭፍጨፋዎች ፡-

በተለያዩ ክልሎች የሚፈጸሙ ጥቃቶች ፡- ከዐማራ ክልል ውጭ በተለይም በኦሮሚያ እና በቤንሻንጉል ጉምዝ ክልሎች በሚኖሩ የዐማራ ተወላጆች ላይ በተደጋጋሚ የማንነት ተኮር ጭፍጨፋዎች እና ግዲያዎች ተፈጽመዋል ።

ጽንፈኛ ታጣቂዎች፡- እንደ ኦነግ ሸኔ (OLA) ያሉ እና ሌሎች የክልሉ አገዛዝ የተለያዩ መጠሪያዎች ሰጥቶ ያደራጃቸውና ያስታጠቃቸው ቡድኖች(ኦነግ ሼነ ፣ አባ ቶርቤ ፣ 120 ፣ ኮሬ ናጌኛ) እና ወዘተ በንጹሃን ዐማራዎች ላይ የሚያደርሱት ጥቃት ለዚህ እንደ ትልቅ ማሳያ ነው ።

2. መጠነ ሰፊ ማፈናቀልና ስደት :-

. **ከቀያቸው ማፈናቀል**:- በሚሊዮን የሚቆጠሩ የዐማራ ተወላጆች በኦሮሚያ ክልል ለዘመናት ከኖሩበት ቀያቸው እንዲፈናቀሉ፣ ንብረታቸው እንዲወድም እና የሀገር ውስጥ ተፈናቃይ (IDP) ሆነው ካምፖች ውስጥ ለአስከፊ ኑሮ እንዲዳረጉ ሆነዋል።

. **የመኖር መብታቸውን መግፈፍ** :- በሕገ-መንግሥቱ የተቀመጠው የብሔር ፌዴራሊዝም ሥርዓት ዐማራዎችን በሌሎች ክልሎች እንደ "መጤ" ወይም "ሰፋሪ" እንዲቆጠሩ ስላደረጋቸው የመኖር መብታቸው ተገፎ ለግዲያና ለስደት ተዳርገዋል።

3. የፖለቲካና ህገመንግሥታዊ ትርክቶች (Anti-Amhara Narratives)

. ላለፉት 50 እና 60 ዓመታት በሀገሪቱ ጽንፈኛ የትግራይና የኦሮሞ ሊህቃን ዘንድ "ዐማራው የቀደሙትን ሥርዐቶች የገነባ ጨቋኝ ነው" የሚል ትርክት ሰለባ ሆኗል ።

. **የሕግ ከለላ መንፈግ**:- ይህ ትርክት ሌላው ሕዝብ በዐማራ ላይ ጥላቻ እንዲያድርበት እና የዐማራ ተወላጆች ጥቃት ሲደርስባቸው የመንግሥት መዋቅር ተገቢውን ጥበቃ እንዳያደርግላቸው ምክንያት ሆኗል ።

4. የወሰን ጥያቄዎች :-

. **የማንነት እና የድንበር ውዝግብ**:- ወልቃይት፣ ጠገዴ፣ ጠለምት እና ራያ የዐማራ ታሪካዊ መሬቶች ቢሆኑም፣ ህወኃት መንበረ ስልጣኑን በቆጣጠር ቀደም ሲል ከነዋሪው ሕዝብ ፍላጎት ውጭ ወደ ትግራይ ክልል መካተታቸውና በሕዝቡ ላይ የደረሰው የባህልና የማንነት ማጥፋት ዘመቻ አንዱ ህልውና አደጋ አካል ነው ። በመሆኑም አሁንም ድረስ የጦርነትና አለመረጋጋት መነሻ ሆኖ ቀጥሏል።

5. ወቅታዊው የክልሉ የጦርነት ቀውስ :-

. **የአገዛቅዙ እና የፋኖ ውግያ** :- የአብይ አህመድ የብልጽግና አገዛዝ የክልል ልዩ ኃይሎችን ለማፍረስ በወሰደው ውሳኔ ማግስት፣ እስከ አፍንጫው የታጠቀውቅን የኦሮሚያ ክልል ልዩ ኃልን እና ሌሎችን ሳይነካ የዐማራን ልዩ ኃይል ለማፍረስ ወደ ዐማራ ክልል የሀገር መከላከያ ሠራዊትን (ENDF) በማዝመቱ ከዐማራ ፋኖ ጋር የጀመረው ከፍተኛ ጦርነት እስካሁን ቀጥሏል ።

. **የሰብአዊ መብት ጥሰቶች**:- በጦርነቱ ምክንያት በክልሉ የሚፈጸሙ የሰው አልባ ድሮን ጥቃቶች፣ ከሕግ ውጭ የሆኑ ግድያዎች ፣ የእንቅስቃሴ ገደቦች ፣ የመሰረተ ልማት መሰረቶች ውድመት ፣ አስገድዶ መድፈር ፣ የጦር ወንጀሎች እና በሺዎች የሚቆጠሩ ዜጎች በጅምላ መታሰራቸው የሕዝቡን የዕለት ተዕለት ሕልውና አደጋ ላይ ጥሎታል።

የዐማራ ሕዝብ የህልውና አደጋ ተዋኒያን እና መሰረታዊ መንስኤዎች :-

የዐማራን ሕዝብ የህልውና አደጋ ምንስኤውችና ተዋኒያንን በተመለከተ የታሪክ ተመራማሪዎች ፣ የፖለቲካ ልሂቃን እና የሰብአዊ መብት ተሟጋቾች በሚከተሉት ዋና ዋና ነጥቦች ይተነትኑታል :-

1. የዘውግ ፌዴራሊዝም ሥርዓት እና ሕገ-መንግሥቱ

. **ህጋዊነትን የተላበሰው ትርክት**፡ እ.ኤ.አ በ1995 የጸደቀው ሕገ-መንግሥት እና የብሔር ተኮር ፌዴራሊዝም ሥርዓት የዐማራን ሕዝብ እንደ "ጨቋኝ" አድርጎ በመሳል፣ በማንነቱ ምክንያት እንዲገለልና ጥቃት እንዲሰነዘርበት ሕጋዊና ፖለቲካዊ መሠረት ጥሏል።

. **የተወካይ አልባ ማድረግ**፡ በሥርዓቱ ውስጥ የዐማራን ሕዝብ መብትና ደህንነት በብቃት የሚያስጠብቅ ፖለቲካዊ ኃይል እንዳይኖር ተደርጓል። በተለይም ከዐማራ ክልል ውጭ የሚኖረው ሕዝብ በሚኖርበት ክልል የመምረጥና የመመረጥ መብት የለው ለምሳሌ በኦሮሚያ ክልል በግምት 5 ሚሊዬን ዐማራ እንደሚኖር ይታወቃል ነገር ግን በክልሉ ውስጥ

በኗርነቱ ግጼታውን ከመወጣት በዘለለ መብቱ አይጠበቅለትም (መምረጥ እና መመረጥ) አይችልም ይባስ ብሎ የመኖር መብቱን ጭምር ተነፍጓል ።

2. የማንነትና የድንበር ጥያቄዎች (ወልቃይትና ራያ)

. የመሬት መወሰድ፡ በኢሕአዴግ/ሕወሃት የሥልጣን ዘመን ወደ ትግራይ ክልል የተካለሉትን የወልቃይት፣ ጠገዴ፣ ሁመራ እና የራያ አካባቢዎችን የዐማራ ሕዝብ ታሪካዊ መሬቶቹ ናቸው። በሴመኑ ጦርነት ወቅት ባለቤቶቹ መልሰው የወሰዱት ቢሆንም ዳግም በመውሰደ ትግራይን እንደ አገር እንመሰርታለን ብለው ጦርነት ጀምረዋል። የብልጽግናው አገዛዝ የሥልጣን ዘመኑን ለማርዘም በህወኃትና በፋኖ መካከል ጦርነት ቀስቅሶ ለማዳከም ያለ የለለ ኃይሉን አሰልፎ ጦርነት በማካሄድ ላይ ይገኛል ። አብይም ሆነ ህወኃቶች ራሳቸውን ችለው ለመዋጋት የአቅም ውስንነት ስላለባቸው ፋኖን እንደ ጆከር ለመጠቀም በሯሯጥ ላይ መሆናቸውን መገንዘብ ይቻላል ። የፋኖ ውሳኔ ምን ይሆናል የሚለውን የምናየው ይሆናል።

በራሴ ቢሆን መልካም ነው የሚለው ፋኖ ከማንኛቸውም ጋር ሳይዋዋል(ሳይጣመድ) በሁለቱ በብልጽግና እና በህወኃት መካከል የሚካሄደው ጦርነት የዐማራን ክልል የጦር ሜዳ እንዳያደርጉት ነቅቶ መጠበቅ እና መከላከል ፣ በሁለቱ (በብልጽግና እና በህወኃት) መካከል የሚካሄደው ጦርነት የአገዛዙን የኃይል ሚዛን ሊያዛባ ስለሚችል ፋኖ አጋጣሚውን ተጠቅሞ የዞታውን በማስፋትና መከላከያን ከክልሉ ለማስወጣት የተቀናጀ ውጊያ ማካሄድ ቢችል መልካም ይመስለኛል።

. የፕሪቶሪያው ስምምነት፡ የፌደራል መንግሥቱ ከሕወሃት ጋር ባለቤቱን የዐማራ ሕዝብ ያላካተተ „የሰላም ስምምነት“ እነዚህን ይዞታዎች አሳልፎ ይሰጣል በሚል በዐማራ ማህበረሰብ ዘንድ ከፍተኛ የስጋትና የመካድ ስሜት ፈጥሯል።

3. ብሔር-ተኮር ጥቃቶች እና መፈናቀሎች

. የሕዝብ መፈናቀል፡ በተለያዩ ጊዜያት (በተለይም በኦሮሚያ ክልል፣ በመተከልና በቤኒሻንጉል ጉሙዝ) በዐማራ ተወላጆች ላይ የተፈጸሙ ስልታዊ ግድያዎች፣ የንብረት ውድመቶች እና የጅምላ መፈናቀሎች ማህበረሰቡ የመንግሥት ጥበቃ እንደሌለው እንዲያውቅ አድርጎታል።

. የአዲስ አበባ ከበባ ሥጋት፡ ወደ አዲስ አበባ የሚገቡ የዐማራ ተወላጆች ክልከላ እና በከተማዋ ዙሪያ (በቀድሞው ሸገር ከተማ) የተካሄዱ ዘር ተኮር መፈናቀሎች ሥጋቱን አባብሰውታል።

. ወታደራዊ እርምጃ፡ በ2015 ዓ.ም (እ.ኤ.አ 2023) የፌደራል መንግሥቱ የክልል ልዩ ኃይሎችን ለማፍረስ በሚል ሽፋን የወሰደው እርምጃ፣ ዐማራው ራሱን ከጥቃት የሚከላከልበትን መዋቅር የማሳጣት ስልታዊ አካል መሆኑን የዐማራ ሕዝብ መገንዘብ።

. የፋኖ ትግልና የድሮን ጥቃቶች፡ ይህንን ተከትሎ በፋኖ ታጣቂዎች እና በፌደራል መከላከያ ሠራዊት (ENDF) መካከል የተቀሰቀሰው ጦርነት፣ በክልሉ ንጹኃን ዜጎች ላይ ያደረሰው የድሮን ጥቃት፣ የጅምላ እስራትና ሰብአዊ መብት ጥሰቶች የህልውና አደጋውን ይበልጥ አግዝፈውታል።

የህልውና አደጋው ዋና ተዋኒያን እነ ማን ናቸነው?

በማህበረሰቡ ዘንድ እነዚህን አደጋዎች ያመጡ ወይም ያባባሱ ተብለው የሚታወቁ አካላት፡-

1. ሕወሃት እና አነጎች ፡ ሥርዓቱን እና ህገ መንግሥቱን በመቅረጽ ፣ ትረካውን ሕዝባዊ በማድረግ እና በማስተግበር ግምባር ቀደሞች ናቸው ።

2. የአሁኑ የፌደራል አገዛዝ (ብልጽግና ፓርቲ)፡ የዐማራን ሕዝብ ለመፍጀት፣ ልዩ ኃይሉን በመበተን እና በክልሉ ወታደራዊ ዘመቻ በማካሄድ ላይ ይገኛል።

3. ጽንፈኛ የብሔረሰብ ታጣቂዎች፡ በተለያዩ ክልሎች በንጹኃን ዐማራዎች ላይ ዘር እና ዕምነት-ተኮር ጥቃት በመፈጸም ላይ ያሉ አገዛዙ ያስታጠቃቸው ሽብርተኖችም የዐማራው የህልውና አደጋዎች ናቸው ።

በአጠቃላይ ለዐማራው የህልውና አደጋ መንስኤ ህወኃትና በአምሳሉ የፈጠራቸው ብልጽግና እና መሰል ጸረ ዐማራ ድርጅቶች ፣ በዐማራው ሕዝብ ላይ የፈጠሩት ሥርዓታዊ የፖለቲካ መገለል፣ የተዛቡ የታሪክ ትረካዎች ፣ የሰላም ዋስትና ማሳጣት እና የወሰን/የማንነት ጥያቄዎች በአግባቡ አለመመለሳቸው ናቸው።

የህልውና አደጋው መፍትሔ ፦

የህልውና አድጋው መንስኤና ተዋኒያን እነ ማን እንደሆኑ ከላይ በግልጽ ስለ ተቀመጠ ህልውናውን ለመታደግ እየተዋደቀ ያለው የዐማራ ፋኖ በሽታውን (መንስኤውን) ለማከም መውሰድ ያለበት ማስታገሻ ሳይሆን መፈወሻ መድሃኒት መሆን አለበት ። መምህርት እና የሰብአዊ መብት ተሟጋች ወይዘሮ መስከረም አበራ እንዳለችው "የዐማራ ሕዝብ ይህንን ጦርነት ማሸነፍ አለበት ፣ ከተሸነፈ ግን ባሪያ ሆኖ ለመኖር እንኳን አይፈቀድለትም" ።

የዐማራ ፋኖ ያለ ድርጅት ዘምቶ አፋብንን የሚያክል ትልቅ ድርጅት መስርቷል ፣ ባዶ እጁን ወጥቶ ከጠላት ቀምቶ ትጥቅ በትጥቅ ሆኗል ፣ ጀግንነት ደግሞ የአያት ቅድመ አያቶቹ ነው ስለሆነም መፍትሔው ማሸነፍ እና ማሸነፍ ብቻ ነው ። ማሸነፍ ሲባል በጦር ሜዳ ውጊያ ጠላትን አንበርክኮ የራሱን የጎበዝ ህለቃ ለስልጣን ማብቃትና ተረኛ ሆኖ ሌላውን መግዛት ማለት አይደለም ። ማሸነፍ ማለት የራሱን የስልጣን ኢጎ ጭምር በማሸነፍ የሀገርና የሕዝብን ጥቅም በማስቀደም ስር ነቀቅል ለውጥ በማምጣት በሕዝብ ፈቃድና ውሳኔ ተመርጦ ለስልጣን መብቃት ማለት ነው ።

ለማሸነፍ ደግሞ ፦

1. የዐማራ ሕዝብ እያካሄደ ያለው ጦርነት እራስን የመከላከል ፍትሀዊ ጦርነት በመሆኑ ያለ ጥርጥር ያሸንፋል እያሸነፈም ነው ፣ ነግር ግን መስዋዕትነትን እየከፈለ ያለው የዐማራ አርበኛ አንድነቱን አጠንክሮ በአነስተኛ ዋጋ ለማጠናቀቅ ውስጣዊ አንድነቱ እንዲጠነክር ከሰርጎ ገቦች የጸዳ መሆን አለበት ።

2. ለአንድ ዓላማና ግብ የተሰለፉ ታጋዮች መደራጀት ፋይዳው ኃይልን አስተባብሮ ወጥ በሆነ የእዝ ሰንሰለት ተቀናጅቶና ተናቦ ጠላትን በአነስተኛ መስዋዕትነት ድል መንሳት ነው ። ስለሆነም የዐማራ ፋኖ ብሔራዊ ንቅናቄ (አፋብን) ድርጅታዊ መዋቅሩን እስከ ታች የመዘርጋት ስራ ጊዜ የማይሰጠው በመሆኑ አመራራሩ ቅድሚያ ሰጥቶ ማጠናቀቅ ይኖርበታል ።

3. የዐማራ ፋኖ የሚታገለው የዐማራን ሕዝብ የህልውና አደጋ ለአንዴና ለመጨረሻ አስወግዶ የኢትዮጵያን ሏላዊነትና የሕዝቦቿን አንድነት ለማረጋገጥ በመሆኑ ዓላማና ግቡን የሚደግፉ ድርጅቶችም ሆኑ ግለሰቦች ጋር በህብረት ለመስራት ይረዳ ዘንድ አፋብን የመታገያ ሰነዱን (Roadmap) ይፋ ማድረግ ይኖርበታል ።

4. የዐማራ ፋኖ (ሕዝብ) ብቻውን ታግሎ እና አሸንፎ ስር የሰደደውን የሀገራችንን ችግር በመፍታት ዲሞክራሲያዊ ስርአት ሊመሰርት አይችልም ስለሆነም የችግሩ ባለቤት ከሆነው ሕዝብ እና ድርጅቶች ጋር በማበር ወይንም በመጣመር አብሮ መስራት የጊዴታ ውዴታ ነው ፣ ያ ማለት ግን እንደ ጅል ህጻን በአንድ እባብ ሁለት ጊዜ ይነከስ ማለት አይደለም ። ስለ ሆነም ጥቂት የፋኖ አመራሮች **ህወኃትን** የመሰለ ጊዜ የማይቀይረው ቆሞ ቀር ድርጅት ጋር ለመጣመድ የሚያደርጉት ሙከራ መዘዙ የከፋ ስለሚሆን ሊያስቡበት ይገባል ።

ህወኃት በዐማራ ሕዝብ ላይ ለፈጸመው የዘር ፍጅት ሌላው ቢቀር እውቅና ሰጥቶ ለአፍ እንኳን የቅርታ ሳይጠይቅ ፣ የባስ ብለው ከዐማራ የቀማውን መሬት ምዕራብ ትግራይ ብለው የከለሉትን በአደባባይ ይዘን እንገነጠላለን እያሉ ፈትለወርቅ (ሞንጀሪኖ) በራሳቸው ሚዲያ በትግርኛ ቋንቋ እና የሳልሳዊ ወያኔ ፓርቲ ሊቀመንበር ገ/ትንሳኤ ወ/ ሚካኤል በርዕዮት ሚዲያ በአደባባይ እየነገሩን ጥምረቱ ለሕዝባችን ምን ጥቅም ሊያመጣ ነው?

እኔ አውቅልሀለሁ በሚል እብሪት በተወሰኑ ግለሰቦች ከተዋጊ አርበኞች እና ከዐማራ ሕዝብ ጀርባ የሚደረግ ማንኛውም ጥምረት ውድ ዋጋ ስለሚያስከፍል ከውጭም ሆነ ከውስጥ ሆነው ወደ ጥፋት ከሚገፉ በዐማራ ስም ከተቋቋሙ ተከፋይ ሚዲያዎችና ምሁር ነን ባይ ሳልሳዊ ብአዴኖች መጠንቀቅ ያስፈልጋል።

5.የዐማራ ሕዝብ እንደ ዐይን ብሌኑ የሚሳሳላቸው ህልውናውን ለመታደግ የሚዋደቁ ልጆቹ (ፋኖዎች) እስከ አፍንጫው የታጠቀውን ጨፍጫፊ የአብይ አገዛዝ ሰራዊት ያሽመደመደው ትጥቁ ፣ ስንቁና ምሽጉ ሆኖ የሚደግፈው ነጻ ያወጣኛል ብሎ በመሆኑ የፋኖ አመራሮች የምትወስኗቸው ውሳኔዎች ሕዝቡን የሚከፋፍል ፣ ተስፋ የሚያስቆርጥ ፣ በማን አለብኝነት የግለሰብን ውሳኔ በመስጠት ትግሉ ከደረሰበት የአጥቂነት ማማ እንዳይወርድ እንደ አንድ ጉዳዩ የሚያስጨንቀው ዐማራ ጥንቃቄ እንድታደርጉ አደራ እላለሁ ።

ድል ለዐማራ ሕዝብ (ፋኖ)

ክብር ለሰማዕታት

ንጉሤ አሊ